# ሞት አንዴ ነው

## ከሞት አይፈሬ፤ ኖርዌይ

አማራ ትግሬ ኦሮሞ
ቢለን ሻንቅላ ጋሞ
አገው ሱማሌ … ሁሉ አድሞ
ለአንዲት ሰንደቅ በአንድ ቆሞ
ለኢትዮጵያ ክብር ቆሞ
ድል እንዳልነሳ ደጋግሞ
        ምነው ዛሬ በእኛ ጊዜ በእኛ ትውልድ
        አገራችንን የምናፈርስ የምንንድ
        የምንሸፍጥ የምንክድ
        በእኛነታችን የምንነግድ
        በሕልውናችን የምንቀልድ
        በአባቶቻችን ያልታየ የሌለ ጉድ
        የምንፈራ የምንርድ
        መሆናችን የሳት ልጅ አመድ
ለእኛነታችን መለያ
የእትብታችን መቀበሪያ
በሕይወት ሳለን መጠለያ
በክብር የአፅማችንም ማረፊያ
የሆነችው አብሲኒያ
የዛሬዋ ኢትዮጵያ
ብሶት በዝቶባት ትጨሃለች
የጀግና ያለህ ትልሃለች
መልሱን በአፋጣኝ ትሻለች
ሕልውናዬን አድን እያለች
        ስለዚህ መናገሩን ትተን ስሞታ
        እኛው በእኛው መላ እንምታ
        አናቅማማ አንከፋፈል አናመንታ
        አለብንና የትውልድ ግዴታ
        ለታሪክ ስንል ለሕዝባችን ከበሬታ
        ደሞ ሰላም ያለ በጥይት ከተመታ
        ምላጩ ይሳብ ይፍልቀቅ ቃታ
        አገር በዋዛ እንዳይፈታ
        ሞት አንዴ ነው እንሙታ!!

-------------------------------------------------------

TPLF and EPLF cannot be reformed,
like apartheid, they should be abolished!